

## ❧ 15 ☙

# መታዘዝ የበረከት ምንጭ ነው

15-1

መታዘዝ የሰማያዊ በረከት ዓይነተኛ ምንጭ ሲሆን፥ አለመታዘዝ ደግሞ የእግዚአብሔር እጅ በልጆቹ ሕይወት እንዳይሠራ እንቅፋት ይሆናል። "መታዘዝ ከመስዋዕት፣ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል" (ሳሙ. ቀዳማዊ 15፥22)።

የሰው ልጅ እግዚአብሔርን "አልታዘዝም" ማለትን የጀመረው አስቀድሞ ምድረ ገነት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ሰው መነካት ያለበትንና የሌለበትን በማስጠንቀቅያ ለይቶ ሰጠው። ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጣሰ። በእርሱም አለ መታዘዝ ምክንያት ኃጢአት በሰው ዘር ሁሉ ላይ እንደ ካንሰር ተሠራጨ። "በአንድ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ" (ሮሜ 5፥19)። በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ኃጢአት እንደ ተላላፊ በሽታ በሰው ዘር ሁሉ ተስፋፋ። ይህ በአለመታዘዝ ምክንያት የመጣው ኃጢአት የሰውን ሕይወት ቦርቡሮ ከእግዚአብሔር ፊት ያለጸጋ አስቀረው። እንግዲህ አስከፊው የሆነው የሰውን መጨረሻ ሊለውጥ የሚችለው የእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ ብቻ ነው።

## መታዘዝ የበረከት ምንጭ ነው

"ቃሉን ብትሰሙ በእግዚአብሔርም ትዕዛዝ ላይ ባታምጹ እናንተና በእናንተ ላይ የነገሠው ንጉሥ አምላካችሁን እግዚእብሔርን ብትከተሉ መልካም ይሆንላችኋል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰሙ፣ በእግዚአብሔርም ትዕዛዝ ላይ ብታምጹ፣ በእናንተና በንጉሣችሁ ላይ የእግዚአብሔር እጅ ትሆናለች" (1ኛ ሳሙ 12፥14-15)። በዚህ ቃል መሠረት የበረከትና የመርገምን ምክንያት ግልጽ በሆነ ሁኔታ መረዳት እንችላለን።

## ያለመታዘዝ ውጤት

በሉሲፈር ሕይወት ውስጥ ኩራት በገባበት ወቅት፥ በእግዚአብሔር ላይ አመጸ። ክብሩንም ተመኘ። በዚህም ምክንያት ሉሲፈር ከሰማያዊ ክብሩ ወርዶ ወደ ምድር ተጣለ። ከምድር የተጣለው ሉሲፈር ኃጢአተኛ የሆነውን ሰው ባለመታዘዝ መንፈስ እግዚአብሔርን እንዲያሳዝን የብዙዎችን ልብ ማሳቱን ቀጠለ። ሳኦል በጥቂት ወታደሮች ጠላቶቹን በጦር ሊወጋ ሲወጣ (ሳሙኤል ቀዳ. 13)፥

1) ግልጽ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር። "አሁንም ቁም እግዚአብሔርም በዓይናችሁ ፊት ወደሚያደር ገው ወደዚህ ታላቅ ነገር ተመለከቱ" (ሳሙ. ቀዳ. 12፥16)። "እግዚአብሔር ለእርሱ ሕዝብ ያደርጋቸው ዘንድ ወድዷልና እግዚአብሔር ስለ ታላቅ ስሙ ሕዝቡን አይተውም (ሳሙ. ቀዳ.

12፥22)። "ነገር ግን ክፉ ብትሠሩ እናንተም ንጉሣችሁንም ትጠፋላችሁ" (ሳሙ. ቀዳ. 12፥15)። የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ሕግ ውስጥ ራሱን መምራት ቢችል የሚያገኘውን በረከት ከመስመር ቢወጣ ደግሞ የሚያጋጥመውን ጥፋት በግልጽ ተነግሮ እናያለን።

2) እግዚአብሔር ለሳኦልና ለወታደሮቹ የሰጠው ትዕዛዝ ቆዩ "ቁሙ" የሚል ነበር። ሳኦል ግን የፍልስጤማውያን ወታደሮች ቁጥር መብዛት ሲያይ፥ ከእርሱ ጋር የወጡት ወታደሮች ደግሞ በፍርሃት ተይዘው መበታተናቸውን ሲመለከት ዕረፍት አጣ። ሳኦል ለጦርነት ከመውጣቱ በፊት ሳሙኤል መጥቶ የሚቃጠል መስዋዕት እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር። ሳሙኤል ግን እንደ ቀጠሮው በወቅቱ ሳይመጣ ሲቀር፥ ራሱ ሳኦል የሚቃጠለውን መስዋዕት አሳረገ። የሚቃጠለውን መስዋዕት ልክ አሳርጎ እንደፈጸመ ሳሙኤል መጣ። ሳሙኤልም በሳኦል አለመታዘዝ አዝኖ እንደ ዚህ አለው። "አላበጀህም፤ አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘህን ትዕዛዝ አልጠበቅህም፤ ዛሬ እግዚአ ብሔር መንግሥትህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጽንቶልህ ነበር። አሁንም መንግሥትህ አይጸ ናም እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነ ሰው መርጦአል፤ እግዚአብሔር ያዘዘህን አልጠበቅህምና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ አዝዞታል" አለው (ሳሙ. ቀዳ. 13፥13-14)።

3) ሳኦል ንጉሥ እንጂ ካህን አልነበረም። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ለማግኘት ሲል መስዋዕት ይዞ ቀረበ። እግዚአብሔር ግን መስዋዕቱንና እርሱን አልተቀበለም። በራስ ፈቃድ የተሞላ አምልኮት ስጋዊ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋን አያስጥም። ሳኦል ለምን እንዳልታዘዘ ምክንያት ለመስጠት ቢሞክርም፥ ምክንያቱ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም።

4) "ሳልታገሥ የሚቃጠለውን መስዋዕት አሳረግሁ" (ሳሙ ቀዳ 13፥12) አለ ሳኦል። ሳኦል ትዕግ ሥት በማጣቱ ምክንያት እግዚአብሔርን እንዳሳዘነው አምኗል። "እግዚአብሔር ስለ ታላቁ ስሙ ሕዝቡን አይተውም" የሚለውን ተስፋ ሳኦል አምኖ መቆም ሲያቅተው ከእግዚአብሔር ሕግና ትዕዛዝ መውጣት ቻለ። ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ጥሶ መሄድ ታላቅ አወዳደቅን ያመጣል። ሳኦል ባለመታዘዙ ምክንያት የንጉሥነት ዙፋኑንና ዘውዱን አጣ። ሳኦል ባለመታዘዙ ምክንያት የደረሰበት ውድቀት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ የሆነው ለትምህርታችን ነው። "መታዘዝ ከመስዋዕት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል" የሚለው ቃሉ በመታዘዝ ውስጥ የሚገኘውን በረከት ያሳየናል።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**